# በትራንስፖርት ሚኒስቴር
# የትራንስፖርት ባለሥልጣን

## ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች ደኅንነት የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎትአሰጣጥን ለመቆጣጠርየወጣ መመሪያ ቁጥር 668/2013

ነሐሴ2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ



አብዲሣ ያደታ ሙለቃ
ዋና ዳይሬክተር

## <u>መግቢያ</u>

የሀገሪቱን የትራንስፖርት አቅርቦትና ፍላጐት በማሟላት ረገድ መከናወን የሚገባው ፈርጀ-ብዙ ተግባር የመኖሩን ያህል በአገልግሎት አሰጣጡም በኩል አሁን ያለውን የተሽከርካሪ አቅርቦት በብቃትና በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል በዘርፉ የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ትኩረት የመስጠት አስፈላጊነቱ የጐላ ነው፡፡

የመንገድ ትራፊክ ደኅንነትን በማረጋገጥ በኩል የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣንና በየደረጃው ያሉ የትራንስፖርት ቅርንጫፍ መ/ቤቶች እንዲሁም የክልል እና የከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮዎች ለዘርፉ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በጋራ እየሰሩ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ ተግባራዊ ጥረቶች መካከል የተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ደኅንነት በማረጋገጥ ረገድ በስፋት እየተስተዋለ ያለውን የትራፊክ አደጋን የመቀነስና ህብረተሰቡም ደኅንነቱ የተጠበቀ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ በኩል ባለፉት ዓመታት የተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የቴክኒክ ብቃት ምርመራ ሥራ ለግል ድርጅቶች ተሰጥቶ በተሻለ ብቃት እና በዘመናዊ መሣሪያ ተደግፎ መከናወን ያለበት በመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶ ባለሀብቶች ውክልና ወስደው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡

ይሁን እንጂ በተሽከርካሪ የቴክኒክ ጉድለት ምክንያት የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋ ከመቀነስም ሆነ የተገልጋዩን ህብረተሰብ ምቾትና ደኅንነት ከማረጋገጥ አንፃር የተሻለ ለውጥ ማምጣት አልተቻለም፡፡ ለዚህም እንደ ዋነኛ ምክንቶች ከሚወሰዱት ውስጥ ውክልና የወሰዱ የምርመራ ተቋማት ኃላፊነት በጎደለው መንገድ የወጣውን ስታንዳርድ ጠብቀው አለመስራት፣ ውክልና ሰጪው አካል የሚያደርገው የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ማነስ፣ የምርመራ ተቋማትን ለማደራጀት፣ ለመደገፍ፣ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የወጣው መመሪያ ቁጥር 04/2004 የነበሩበት የግልፅነት፣ የተጠያቂነትና የትግበራ ውስንነቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም እስካሁን የነበረውን ጅምር የሥራ ጥረት በማጠናከር የሚሰጠውን አገልግሎት ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን ከነበሩ የሥራ ልምዶችና ከሚስተዋሉት አንዳንድ የአሰራር ችግሮች አንፃር የተሟላ ሁኔታ በማመቻቸት የውክልና አሰጣጥና ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት በተሟላ አደረጃጀት የተደገፈ፣ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

ያካተተ ሥርዓት እንዲኖር ለማስቻል ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀጽ 49/2/ መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ፤**

ይህ መመሪያ ‹‹ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች ደኅንነት የቴክኒክ ምርመራ አሰጣጥን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁጥር 668/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይች

2. **ትርጓሜ፤**

1) በአዋጅ ቁጥር 468/1997 እና በአዋጅ ቁጥር 681/2002 ትርጓሜ የተሰጣቸው ቃላት እንደ አግባብነታቸው በዚህ መመሪያም ተፈፃሚ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2) **‹‹ቅርንጫፍ ትራንስፖርት መ/ቤት››** ማለት በአዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 26 ነዑስ አነቀጽ 2 መሰረት በፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ስር በቅርንጫፍ መ/ቤትነት እንዲሠሩ የተደረጉት ማለት ነው፡፡

3) **‹‹የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት››** ማለት ዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራን ለፈፀመ ተሽከርካሪ ምርመራውን በአከናወነው የምርመራ ተቋም የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡

4) **‹‹የተመረመረ ተሽከርካሪ››** ማለት ተሽከርካሪው በምርመራ ተቋም ተገኝቶ በእይታ እና በማሽን ላይ እያንዳንዱን የምርመራ ሂደቶች ሙሉ በሙሉ አከናውኖ ስለማለፉ የሚገልፅ የምስል እና የጽሑፍ መረጃ በተቀናጀ ሁኔታ በዳታ ቤዝ ውስጥ ያለው ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

5) **‹‹ያልተመረመረ ተሽከርካሪ››** ማለት ተሽከርካሪው በምርመራ ተቋም ውስጥ የምርመራ ሂደት ስለማለፉ የሚገልፅ የምስል እና የጽሑፍ መረጃ በተቀናጀ ሁኔታ በዳታ ቤዝ ውስጥ የሌለው ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡



አብዲሣ ያደታ
ዋና ዳይሬክተር

6) «**የቴክኒክ ምርመራ ማንዋል**» ማለት የተሽከርካሪ የቴክኒክ መርማሪ ባለሙያዎች ማወቅ የሚገባቸውን የመመርመሪያ መሳሪያዎችን፣ የመመርመሪያ ቼክ ሊስት፣ የስራ ሂደቱን ተግባራት፣ ሥራው የሚፈጀው ጊዜና የሥራ ፍሰቱን ቅደም ተከተልና የመሳሰሉትን በሚገልፅ መልኩ በጽሑፍ የተዘጋጀና በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ የሥራ ማከናወኛ ሰነድ ማለት ነው፡፡

7) «**የቴክኒክ ምርመራ መሣሪያዎች**» ማለት ብቃታቸው በዕይታ ብቻ ሊታወቁ የማይችሉ የተሽከርካሪ አካላትንና ልዩ ልዩ ክፍሎችን ያሉበትን የቴክኒክ አቋምና ብቃት ማወቅ እንዲቻል ለተሽከርካሪ ምርመራ የሚያገለግሉ የመለኪያ መሣሪያዎችን ቁሳቁሶችንና ለምርመራ የሚያገለግሉ መሠረተ ልማቶችን የሚያካትት፤ በቴክኒክ ምርመራ ማንዋል ተንቀሳቃሽ እና ቋሚ ተብለው የተዘረዘሩ መሣሪያዎች ማለት ነው፡፡

8) «**የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የምስክር ወረቀት**» ማለት ዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃትን በምርመራ ለማረጋገጥ የሚያስችል በሥራ ቦታ ተለይቶ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡

9) «**ቋሚ የምርመራ መሣሪያ**» ማለት በተወሰነ የምርመራ ጣቢያ ውስጥ በወለል ላይ ተተክሎ ለዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት የሚውል መሣሪያ ነው፡፡

10) «**ተንቀሳቃሽ የምርመራ መሣሪያ**» ማለት በልዩ ተሽከርካሪ ላይ ተጭኖ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ለዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራም ሆነ ለድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት የሚውል መሣሪያ ነው፡፡

11) «**ተንቀሳቃሽ የእጅ የምርመራ መሣሪያ**»ማለት ከቦታ ወደ ቦታ በእጅ ተይዞ ሊንቀሳቀስ የሚችል ሆኖ ለምርመራ በተሽከርካሪ ላይ ታስሮ ለዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አገልግሎት የሚውል መሣሪያ ነው፡፡

12) «**የሥራ ሪፖርት**" ማለት ከምርመራ መሣሪያዎቹ የሚገኙ የጽሑፍና የምስል ፕሪንት አውት በምርመራ ተቋማት የሚዘጋጁ የሥራ ቅፆችንና በባለሥልጣኑ የሚዘጋጁ የማጠቃለያ ሪፖርትን በሶፍት ኮፒና በሀርድ ኮፒ ፎርማቶች በምርመራ ተቋሙና በባለሥልጣኑ መካከል የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ ነው፡፡

13) «**የሥራ ቅፆች**» ማለት ለዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት አሠጣጥ የሚቀርቡ ተሽከርካሪዎችን ለመቀበልና የምርመራ ሂደቱን ለማከናወን



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

የሚያስችሉ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀ የተሽከርካሪ ምርመራ ቼክ ሊስት እና ቅፆች ናቸው፡፡

14) «**የኮምፒውተር የመረጃ ግንኙነት**» ማለት የሚሰጠውን ዓመታዊ የተሽከርከሪ የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት አፈፃፀም የመረጃ ምንጩ መረጃዎችን ከመዘገበ በኋላ ወደ ማዕከላዊ ዳታ ባንክ በቀጥታ ለማስተላለፍ ወይም ከየርቀቱ ባሉ ኮምፒውተሮች መረጃ ለመናበብና የስራ ሪፖርት ለመለዋወጥ እንዲያስችል በስልክ መስመር ወይም በሌላ መንገድ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡

15) «**መርማሪ ባለሙያ**» ማለት ማንኛውንም ለዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ የሚመጡና አገልግሎት የሚወስዱ ተሽከርካሪዎችን በየደረጃው በዕይታና በዘመናዊ መሣሪያ የቴክኒክ ብቃታቸውን በማረጋገጥ፣ የምርመራ ውጤት የሚሰጥ ሆኖ ይህንን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ሕጋዊ ከሆነ ተቋም የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለው ነው፡፡

16) «**የሙያ ብቃት**» ማለት የተሽከርከሪ የቴክኒክ ምርመራ ሥራን በብቃት ለመወጣት የሚያስችል፣ በመደበኛ የትምህርት ሂደት በሥልጠና ጭምር የተደገፈና በባለሥልጣኑ በተቀመጠው አነስተኛ ተፈላጊ የሙያና የክህሎት መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ለአንድ ሰው የሚሰጥ የሥራ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ነው፡፡

17)«**የምርመራ ተቋም**» በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 18 እስከ 21 ድረስ በተደነገገው መሠረት የተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ብቃት በምርመራ አረጋግጦ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

18) «**ደረጃ አንድ (አነስተኛ) ተሸከርካሪ የምርመራ ተቋም**» የባለ ሁለት እና ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪዎችን እና ጠቅላላ ክብደታቸው እስከ 450 ኪሎ ግራም የሚደርስ ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ብቃት በምርመራ አረጋግጦ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

19)«**ደረጃ ሁለት (ቀላል) ተሸከርካሪ የምርመራ ተቋም**» ማለት ጠቅላላ ክብደታቸው 450 እስከ 3,500 ኪሎ ግራም የሚደርስ ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ብቃት በምርመራ አረጋግጦ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

20) «**ደረጃ ሶስት (መካከለኛ) ተሸከርካሪ የምርመራ ተቋም**» ማለት ጠቅላላ ክብደታቸው ከ450 ኪሎ ግራም እስከ 7,500 ኪሎ ግራም የሚደርስ

ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ብቃት በምርመራ አረጋግጦ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

21)‹‹**ደረጃ አራት (ከፍተኛ) ተሽከርካሪ የምርመራ ተቋም**›› ማለት ጠቅላላ ክብደታቸው ከ 450 ኪሎ ግራም በላይ የሚመዝኑ ተሽከርካሪዎችን እንዲሁም ባለሞተር ጎታችና ግማሽ ተሳቢ እና ከባድ ካሚዮንና ተሳቢን የቴክኒክ ብቃት በምርመራ አረጋግጦ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

22) ‹‹**ድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ**››ማለት የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት በተቀመጠላቸው ስታዳርድ፣ የአገልግሎት ጥራት እና ሥራው የሚጠይቀውን የሙያ ሥነ-ምግባር ተከትለው እየሠሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች የሚደረግ ከቋሚ ፕሮግራም ውጪ ወይም ድንገተኛ የምርመራ ዓይነት ነው፡፡

23) ‹‹**ልዩ ምርመራ**››ማለት ተሽከርካሪው ተመርምሮ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እና ተለጣፊ ቦሎ ከወሰደ በኋላ በመንገድ ላይ የተሽከርካሪውን ብቃት ለማረጋገጥ የሚደረግ የምርመራ ዓይነት ነው፡፡

## 3. ዓላማ፤

የመመሪያው ዓላማ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ የተቋማት ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አገልግሎት አሰጣጥ ግልፅ ቀልጣፋ እና ጥራት ያለው እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን፤

ይህ መመሪያ በመንገድ ላይ በሚንቀሳቀሱ ማናቸውም ባለሞተር ተሽከርካሪዎች፣ የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋማት፣ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች እና ሹፌሮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡



አብዲሳ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል ሁለት

## የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 5. የባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት፤

1) በየክልሉ ለሚገኙ የምርመራ ተቋማት የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የምስክር ወረቀት መስጠት የሚያስችልና አሠራራቸውን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የውክልና ሥልጣን ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር የትራንስፖርት ቢሮዎች ይሰጣል፡፡
2) የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር የትራንስፖርት ቢሮዎች ለምርመራ ተቋማት የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ስለ ሚሰጡበትና የምርመራ ተቋማትም ሥራቸውን ስለ ሚያከናውኑበት ሁኔታ የሥራ ማንዋል ያዘጋጃል፡፡
3) ለሥራው የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ የሥራ ማከናወኛ ቅፆችን፣ ቸክ ሊስቶችን እና መደበኛ የሥራ ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማቶችን በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙንም ይቆጣጠራል፡፡
4) የዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ሕጋዊ የቆይታ ጊዜ ይወስናል፡፡
5) በፌዴራል ደረጃ ለተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ተለጣፊ ቦሎ ያዘጋጃል፣ ያሳትማል፣ ያሰራጫል
6) ትክክለኛ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ላቀረቡ ተሽከርካሪዎች የዘመኑን ተለጣፊ ቦሎ ይሰጣል ወይም በውክልና እንዲሰጥ ያደርጋል
7) የሚቀርብለትን ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሕጋዊነትና ትክክለኛ ስለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡
8) የተሳሳተ፣ ሕጋዊ ያልሆነና በማስመሰል የተሠራ የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የምስክር ወረቀት፣ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የሙያ ብቃት መረጋገጫ ፈቃድ ሕጋዊ አለመሆኑ ሲረጋጥ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
9) የኮምፒውተር የመረጃ ግንኙነት ስለሚኖረው የመረጃ ልውውጥ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙንም ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፡፡



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ባለሥልጣን
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

10) የምርመራ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጣቸው ጥራት ያለውና ከብልሹ አሠራር የፀዳ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ድጋፍና ክትትልም ያደርጋል፡፡

11) ባለሥልጣኑ ከክልል እና ከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮ የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ወስደው አገልግሎት የሚሰጡ የምርመራ ተቋማት ላይ ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፣ የአደረጃጀት እና የአሠራር ጉድለት ሲገኝ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም እንደ ጥፋቱ ክብደት ለክልሉ ወይም ከተማ አስተዳደሩ የሰጠውን ውክልና ያነሳል፡ የፈቃድ ሰጪና ተቀባይ የሁለቱንም ፈቃድ እንዲሰረዝ ያደርጋል

12) ፍቃድ ሰጪ አካል የምርመራ ተቋሙን የሶፍት ዌር ቁጥጥር እንደ አስፈላጊነቱ ለግል ተቋም በውክልና ይሰጣል፤ ውክልና ከተሰጠው የግል ተቋም በሚገኝ መረጃ ላይም ተመስርቶ በምርመራ ተቋሙ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

13) አገልግሎቱን ለመስጠት ውክልና የተቀበሉ ድርጅቶች ውክልናው እንዲነሳላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ ማመልከቻቸውን በመቀበል ጉዳዩን መርምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መልስ ይሰጣል፡፡

14) ዓመታዊ የተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት አስመልክቶ በየዓመቱ ያለውን የምርመራ ጊዜና የአገልግሎት አሰጣጥ ባለስልጣኑ ፕሮግራም ያወጣል፤ የአገልግሎቱንም አሰጣጥ ለተገልጋዩ ግልፅ ያደርጋል፡፡

15) በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ እንዲውሉ የተዘጋጁትን ልዩ ልዩ መስፈርቶችና መመዘኛዎች በጥናት ላይ የተመሠረተ ማሻሻያ በማድረግ ለየክልል እና ከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮዎች በማሳወቅ አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

16) የማንኛውንም የምርመራ ተቋም ሰነድ ወይም የመመርመርያ ማሽን በመፈተሽ መረጃ መውሰድ ይችላል፡፡

17)የተሽከርካሪ ቴክኒክ ብቃት ማረጋገጥ የሚያስችል የመሳሪያዎች አጠቃቀም ሥልጠና ባለስልጣኑ ከከምርመራ ተቋሙ ጋር በመተባበር በምርመራተቋሙ ማሽን ላይ ማሠልጠን ይችላል፡፡

18) ለምርመራ ተቋም ባለሙያዎች አጫጭር ስልጠና ይሰጣል፡፡

19)በልዩ ሥልጠና ብቃታቸዉን ላረጋገጡ ባለሙያዎች የሙያ ፍቃድ ይሰጣል፤ በሚያደርሱትም ሙያዊ የሥነ-ምግባር ጉድለት እስከ የሙያ ፈቃድ መሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ይወስዳል፡፡



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትራንስፖርት ሚኒስቴር የትራንስፖርት ባለሥልጣን ቁ.1
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

20) የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮ በእስታንዳርዱ መሠረት እውቅና የተሰጠው ተቋም በማንኛውንም ክልል ወይም ከተማ መስተዳድር የተመዘገበ ተሽከርካሪ ምርመራ ማካሄድ ይችላል፡፡

## 6. የክልል እና የከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት፤

ከባለሥልጣኑ ውክልና የተሰጠው ማንኛውም የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮ፡-

1) ዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አገልግሎት ለሚሰጡ የምርመራ ተቋማት የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡
2) ለምርመራ ተቋማት ዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አገልግሎት አከናውነው የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት የሚያስችል የውክልና ሥልጣን ይሰጣል፡፡
3) ዓመታዊ የተሽከርካዎችን የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት እንዲያከናውኑ ለምርመራ ተቋማት እውቅና ይሰጣል፡፡
4) እውቅና ወይም ውክልና የሰጣቸውን የምርመራ ተቋማት ዝርዝር ለባለሥልጣኑ እና ባለሥልጣኑ ፍቃድ ወይም ውክልና ለሰጣቸው ሌሎች የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር ትራንስፖረት ቢሮ እውቅና ያገኙ ስለመሆናቸው ያሳውቃል፡፡
5) የምርመራ ተቋማት በወጣላቸው ስታንዳርድ መሠረት መሥራታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣ በተገኘው ክፍተት ላይ የእርምት እርምጃ በመመሪያው መሰረት ይወስዳል
6) ስለሚሰጠው የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራና አሰጣጥ አስመልክቶም በሚመደቡት የቁጥጥር አገልግሎት ባለሙያዎች የድንገተኛ ምርመራ እንዲደረግ ያደርጋል፡፡
7) ስለሚከናወኑ የተሽከርካሪዎች ድንገተኛ ምርመራ ሂደት አፈፃፀም የመረጃ መመዝገቢያና የሪፖርት ማቅረብያ ፎርማት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
8) በምርመራ ተቋማቱ ለዚሁ አገልግሎት የተመደቡ የምርመራ ባለሙያዎች አስፈላጊውን ትብብር ሁሉ እንዲያደርጉ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡፡
9) የምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ውክልና የተሰጣቸው የምርመራ ተቋማት የስራ ብቃትና አገልግሎት አሰጣጣቸውን በተመለከተ እንደአስፈላጊነቱ ባለሙያዎችን ወደ



Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport Authority No. 1

እብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

ቦታው በመላክ ግምገማና ቁጥጥር ያደርጋል፤ በሚስተዋሉ የአፈፃፀም ችግሮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ የተወሰደውንም እርምጃ ለባለስልጣኑ እና ለሌሎች ክልሎች እና ከተማ መስተዳድር በጽሁፍ ያሳውቃል

10) ዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራና የቦሎ አገልግሎትን አስመልክቶ በየዓመቱ ያለውን የሥራ ጊዜ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ፕሮግራም ለተገልጋዩ በግልፅ በቅድሚያ በማስታወቂያ ይገለፃል፡፡

11)ለአገልግሎት አሰጣጡ እንዲውል በባለሥልጣኑ የተዘጋጁትን ልዩ ልዩ መስፈርቶችና መመዘኛዎች ማሻሻያ ለምርመራ ተቋማቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፤ የምርመራ ተቋማቱም ለተገልጋዮች በግልፅ ማስታወቂያ በቅድሚያ ማስታወቃቸውንና ተግባራዊ ማድረጋቸውን፤ ክትትል ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፡፡

12)ከሐምሌ 15 እስከ መስከረም 15 ቀን ድረስ የምርመራ ተቋማትን አሠራር ዓመታዊ ግምገማ ያካሂዳል፡፡

## 7. የምርመራ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት፤

በባለሥልጣኑ ውክልና ከተሰጠው የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር የትራንስፖርት ቢሮ የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የምስክር ወረቀት የወሰደና እውቅና ያለው ማንኛውም የምርመራ ተቋም፡-

1) ከሚመለከተው የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር የትራንስፖርት ቢሮ ጋር የምርመራ አገልግሎቱን ፍትሐዊ በሆነ መልኩ፣ በጥራትና በተገቢው ቅልጥፍና ለመስጠት የሚያስችል የውክልና ውል ይዋዋላል፡፡

2) የተሽከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ሲያከናውን በተቀመጡት መስፈርቶች፣ በሕግና መመሪያ መሠረት መሆኑን አረጋግጦ መሥራት አለበት፡፡

3) መስፈርት ተብለው በመመሪያው እና በማንዋሉ የተጠቀሱትን ለምርመራ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን በማንኛውም ጊዜ አሟልቶ መስራት ይኖርበታል፡፡

4) በማንኛውም ጊዜና የስራ ሂደት የተለየ ሁኔታ ወይም ችግር ሲያጋጥመው ለውክልና ሰጪው ሪፖርት ማድረግና መመሪያ መጠየቅ ይኖርበታል፤ ውክልና ሰጪው የሚሰጠውን የመፍትሔ አቅጣጫ ችግሮች እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡

5) ለሥራው የሚያስፈልጉትን ቅፆች ከውክልና ሰጪው በሚሰጥ ናሙና መሠረት በራሱ ወጪ በማዘጋጀት ወይም ከውክልና ሰጪው በመግዛት በሥራ ላይ ያውላል፡፡



እብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት ሚኒስቴር የትራንስፖርት ባለሥልጣን ቁ.1
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

6) ባለሙያዎች ባለሥልጣኑ በሚያስቀምጠው ስታንዳርድ መሠረት በመልካም ሥነ-ምግባር እና በቅልጥፍና የምርመራ አገልግሎት መስጠታቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡

7) የሚመለከተው የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር የትራንስፖርት ቢሮ በምርመራ ተቋሙ የሥራ አፈፃፀም ላይ ለሚያደርገው ቁጥጥር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

8) ተገቢውን ሥልጠና ወስደው በቂ እውቀትና ክህሎት ያላቸውን መርማሪ ባለሙያዎችና አስፈላጊ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ የሥራ መልቀቂያ ክሊራንስ ይሰጣል፡፡

9) የተሸከርካሪዎች ዓመታዊ የቴክኒክ መርማሪ ባለሙያን ወደ ሥራ ከማሰማራቱ በፊት ባለሙያው ከሚመለከተው የክልል ወይም የከተማ መስተዳር የትራንስፖርት ቢሮ የሙያ ፈቃድ ወረቀት ማግኘቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

10) ለአንድ ተሸከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ሲሠራለት በቅድሚያ የዕይታ ምርመራን አከናውኖ ማለፉን በማረጋገጥ ወደ ማሽን ምርመራ መግባቱን ይቆጣጠራል፡፡

11)የተሸከርካሪው ደኅንነት በዕይታ ወይም በማሽን ብቻ ምርመራ በማካሄድ ስለማይረጋገጥ በዕይታ እና በማሽን በአንድነት ተመርምሮ የማሽን ውጤት በዳታቤዝ ውስጥ መገኘቱን ያረጋግጣል፡፡

12) በአካል ቀርቦ የቴክኒክ ብቃቱ ለተመረመረ ተሸከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ትክክለኛነት ከባለሙያው ጋር በጣምራ ፊርማና ቲተር እንዲሁም በድርጅቱ ማሕተም መረጋገጥ አለበት፡፡

13) ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ የተደረገላቸውን ተሸከርከሪዎች መረጃ የሥራ ሰነዶች አደራጅቶ ይይዛል፤ ደኅንነታቸውን ይጠብቃል፤ ወደ ባለሥልጣኑ የመረጃ ማዕከልም ያስተላልፋል፡፡

14) በማንኛውም ጊዜ የምርመራ ተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ አስመልክቶ ማብራሪያ እንዲሰጥ በሚመለከተው የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት፣ የክልል ወይም የከተማ መስተዳድድር የትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም ቢሮ በተጠየቀ በሦስት ቀን ውስጥ ተገቢውን ማብራሪያ ይሰጣል፡፡



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

15) ውክልና ሰጪው አካል ስለ ሥራው አፈፃፀም ተገቢውን ክትትል ለማድረግ እንዲያስችለው ባዘጋጀው መርሀ-ግብር እና የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ መሠረት የተሟላ መረጃ በሶፍት ኮፒ እና በሰነድ ሪፖርት አዘጋጅቶ በየወሩ ያቀርባል፡፡

16) በተሽከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ወቅት ስለ ተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ በወጡት ሕጎች መሠረት በተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ ዋና ግልባጭ ላይ የሰፈሩትን ዝርዝር መለያዎች ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡

17) ማንኛውም የተሽከርካሪ ባለቤት ዓመታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ምርመራ እንዲደረግለት ጥያቄ ሲያቀርብ በባለሙያው አማካይነት ተሽከርካሪው የቴክኒክ ጉድለት የሌለው እና ምቾት ያለው መሆኑን በተቀመጠው መመሪያ እና ማንዋል መሠረት የምርመራ ሂደቱን ማለፉን ያረጋግጣል፡፡

18) የቴክኒክ ብቃታቸውን ላረጋገጠላቸው ተሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ይሰጣል፣ የተቋሙን ስም መለያ ተለጣፊ ስቲከር አዘጋጅቶ በተሽከርካሪ ላይ ይለጥፋል፡፡

19) በዚህ መመሪያ በተገለፀው መሠረት የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ምርመራ የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፡፡

20) የሚሰጠውን አገልግሎት አስመልክቶ ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች፣ ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች በወቅቱ ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፡፡

21) ማንኛውም እውቅና የተሰጠው የምርመራ ተቋም የውክልና ውል ተቀብሎ መሥራት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የዳታ ቤዝ የምሥጢር ቁጥር ይያዛል፡፡

22) ለሚሰጠው ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት አሰጣጥ የሚገለገልባቸውን የሥራ ቅፆች በሙሉ ለዚሁ ሥራ ብቻ ያውላል::

23) የምርመራ ተቋሙ የወሰደው የሥራ ውክልና እንዲነሳለት ሲፈልግ በቂ ምክንያቱን በመዘርዘር በአንድ ወር ጊዜ ለውክልና ሰጭው በማሳወቅ መልስ እስከሚሰጠው ሥራውን እያከናወነ መጠበቅ አለበት፡፡

24) ስለ ተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት አሰጣጥ የወጡትን የትራንስፖርት ሕጎች በማክበርና በባለሥልጣኑ የወጣውን መመሪያ እና የሥራ ማንዋል በመቀበል በሥራ ላይ ያውላል፡፡

25) የመድን ሽፋን ከሚሰጥ የኢንሹራንስ ኩባንያ የመድን ሽፋን ዋስትና በመግባት ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት መኖሩን ያረጋግጣል፡፡



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

26) ከክልሉ ወይም ከከተማ መስተዳድሩ የትራንስፖርት ቢሮ የወሰደውን የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የክፍያ ታሪፍ ሌሎች ከመልካም አስተዳደር ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮችን እና ከባለስልጣኑ ወይም ከክልል እና ከተማ አስተዳደሩ የሚሰጡ ሰርኩላሮችን በግልፅ በሚታይ ቦታ ይለጥፋል፡፡

27)ለማንኛውም የመረመራቸው ተሽከርካሪዎች የዘመኑ የታደሰ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፣ የምርመራ ውጤት የሚያሳይ ሰርትፍኬት እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን አያይዞ መላክ አለበት፡፡

28) ውክልና የተሰጠው የምርመራ ተቋም በተለያዩ ቦታዎች ላይ ቅርጫፍ መክፈት ከፈለገ ቅርንጫፉ የሚገኝበትን ክልል ወይም አካባቢ መጠሪያ እና የቅርንጫፍ ቁጥር በቅርንጫፉ ማሕተም ላይ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

29)የፌዴራል፣ የክልል እና ከተማ አሰተዳደር የትራንስፖርት ባለስልጣን እና ቢሮዎች ለሚመጡ ኃላፊዎች፣ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች ተገቢውን መረጃ የመስጠት፣ የማስፈተሽ እና አስፈላጊውን ህጋዊ ትብብር ማድረግ አለባቸው

30)ካሊብሬሽን/ የማሽን እርማት ከሚመለከተው መስሪያ ቤት፣ (ደረጃ ወይም ከስነልክ የመንግስት ተቋማት) የምርመራ ማሽኑ ብቃቱ የተረጋገጠ ስለመሆኑ ማስረጃ በየዓመቱ መቅረብ አለበት፡፡



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

# ክፍል ሦስት

## ለምርመራ ተቋም ውክልና ስለመስጠት፣ ስለ ዕድሳትና ምርመራን ስለማከናወን፣

### 9. ለምርመራ ተቋም ውክልና ስለመስጠት፤

1) ከባለሥልጣኑ ውክልና የወሰደ የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር የትራንስፖርት ቢሮ የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ለሰጠው የምርመራ ተቋም የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ምርመራን ለማከናወን የሚያስችል ውክልና ይሰጣል፡፡

2) የምርመራ ተቋሙ ውክልና ለመውሰድ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤
   - ማመልከቻ፣
   - የሥራ አስኪያጁ/የባለቤቱ/ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ዋናውን እና 1 ኮፒ፣
   - የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የምስክር ወረቀት ዋናውን እና 1 ኮፒ፣
   - የባለይዞታ ካርታ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ የፀደቀ የቤት ኪራይ ውል ዋናውን እና 1 ኮፒ፣
   - በተቋሙ/በባለቤቱ/ ስም የተመዘገበ ዘመናዊ የምርመራ መሣሪያ ዋናውን እና 1 ኮፒ፣
   - የሙያ ብቃት ሰርተፍኬት ዋናውን እና 1 ኮፒ፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የምርመራ አገልግሎቱን ለማከናወን በሚከተለው ሠንጠረዥ ለደረጃው የተቀመጠውን የቦታ ስፋት ስታንዳርድ መሟላት አለበት፡፡

| እስታዳርድ | ደረጃ አንድ (አነስተኛ) | ደረጃ ሁለት (ቀላል) | ደረጃ ሦስት (መካከለኛ) | ደረጃ አራት (ከፍተኛ) |
|---|---|---|---|---|
| የግቢ ስፋት | 60 ካሬ | 250 ካሬ | 300 ካሬ | 450 ካሬ |
| የመመርመርያ ቦታ | ስፋት 2 ሜትር<br>ርዝመት 6 ሜትር | ስፋት 5 ሜትር<br>ርዝመት 14 ሜትር | ስፋት 5 ሜትር<br>ርዝመት 17 ሜትር | ስፋት 7 ሜትር<br>ርዝመት 25 ሜትር |
| የጉድጓዱ ስፋት | የለዉም | ቁመት 4 ሜትር፣<br>ጎን 0.90 ሣንቲ ሜትር ጥልቀት 1.50 ሜትር | ቁመት 7 ሜትር<br>ጎን 0.90 ሣንቲ ሜትር<br>ጥልቀት 1.50 ሜትር | ቁመት 7 ሜ<br>ጎን 0.90 ሣንቲ ሜትር<br>ጥልቀት 1.50 ሜትር |
| ሊፍት | የለዉም | 3,500 ቶን የሚያነሣ | 7,500 ቶን የሚያነሣ | ------- |
| የቢሮ ስፋት | ስፋት 5 ሜትር<br>ርዝመት 6 ሜትር | ስፋት 5 ሜትር<br>ርዝመት 6 ሜትር ጠቅላላ ስፋቱ 30 | ስፋት 5 ሜትር<br>ርዝመት 6 ሜትር ጠቅላላ | ስፋት 5 ሜትር<br>ርዝመት 6 ሜትር ጠቅላላ |



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት ባለሥልጣን
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ጠቅለላ ስፋቱ 30 ካሬ ወይም ሁለት ክፍል | ካሬ ወይም ሁለትክፍል | ስፋቱ 30 ካሬ ወይም ሁለት ክፍል | ስፋቱ 30 ካሬ ወይም ሁለት ክፍል |
| የሀንገር በር | ስፋት 2 ሜትር ከፍታ 2.5 ሜትር | 3 ስፋት ቁመት 4. ሜ | 3 ስፋት ቁመት 4. ሜ | 3 ስፋት ቁመት 4. ሜ |
| የመግቢያ እና መዉጫ በር | 1 በር 2ሜ ስፋት በ2ሜ ቁመት | 1 በር ቁመት 4 ሜ ስፋት 5 ሜ/ 2 በር ቁመት 4 ሜ ስፋት 4 ሜ/ | 1 በር ቁመት 4 ሜ ስፋት 5 ሜ/ 2 በር ቁመት 4 ሜ ስፋት 4 ሜ/ | 1 በር ቁመት 4.20 ሜ ስፋት 7 ሜ/ 2 በር ቁመት 4.20ሜ ስፋት 6 ሜ/ |
| የሚመረምረው የተሽከርካሪ ዓይነቶች | ሞተር ሳይክል፣ ሶስት እግር ተሽከርካሪ እስከ 450 ኪሎግራም ክብደት ያላቸው ተሽከርካሪዎች | • 450 እስከ 3500 ኪሎ ግራም ድረስ የሚመዝኑ ተሽከርካሪዎች | • 450 እስከ 7500 ኪሎ ግራም ድረስ የሚመዝኑ ተሽከርካሪዎች | • ከ450 ኪሎ ግራም በላይ የሚመዝኑ ተሽከርካሪዎች |

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ መመርመሪያ መሣሪያ ለሚሠሩ ተቋማት የሚያስፈልግ ዝቅተኛ የሰው ኃይል ብዛት ከዚህ በታች በሠንጠረዥ በተቀመጠው መሠረት ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | ባለ ሙያ | ደረጃ | ብዛት | የትምህርት ዝግጅት | የሙያ ትምህርት አይነት | ልዩ ስልጠና |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቡድን መሪ | አንድ (አነስተኛ) | 1 | በአውቶሞቲቭ ወይም በመካኒካል ኢንጅነሪንግ የተመረቀ/ች | ዲፕሎማና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያለው/ያላት | • የኮምፒውተር ስልጠና የወሰደ<br>• አፕሩቫል |
| | | ሁለት (ቀላል) | 1 | በአውቶሞቲቪ ወይምመካኒካልኢንጅነሪንግየተመረቀ/ች | ዲፕሎማና ከዚያ በላይ ደረጃ ያለው/ያላት | • የኮምፒውተር ስልጠና የወሰደ<br>• አፕሩቫል |
| | | ሶስት (መካከለኛ) | 1 | በአውቶሞቲቭ ወይም በመካኒካል ኢንጅነሪንግ የተመረቀ/ች | ዲፕሎማናከዚያበላይደረጃያለው/ያላት | • የኮምፒውተር ስልጠና የወሰደ<br>• አፕሩቫል |
| | | አራት (ከፍተኛ) | 1 | በአውቶሞቲቭ ወይም በመካኒካልኢንጅነሪንግየተመረቀ/ች | ዲፕሎማ እና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃያለው/ያላት | • የኮምፒውተር ስልጠና የወሰደ<br>• አፕሩቫል |
| 2 | መርማሪ ቴክኒሽያን | አንድ (አነስተኛ) | 2 | በአውቶሞቲቪ ወይምመካኒካልኢንጅነሪንግየተመረቀ/ች | ሌቭል 3 እና ከዛ በላይ | • ኮምፒውተር ስልጠና<br>• አፕሩቫል |
| | | ሁለት (ቀላል) | 3 | በአውቶሞቲቪ ወይምመካኒካልኢንጅነሪንግየተመረቀ/ች | ሌቭል 3 እና ከዛ በላይ | • ኮምፒውተር ስልጠና<br>• አፕሩቫል |
| | | ሶስት (መካከለኛ) | 3 | በአውቶሞቲቪ ወይምመካኒካልኢንጅነሪንግየተመረቀ/ች | ሌቭል 3 እና ከዛ በላይ | • ኮምፒውተር ስልጠና<br>• አፕሩቫል |
| | | አራት (ከፍተኛ) | 3 | በአውቶሞቲቪ ወይምመካኒካልኢንጅነሪንግየተመረቀ/ች | ሌቭል 3 እና ከዛ በላይ | • ኮምፒውተር ስልጠና<br>• አፕሩቫል |



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | መረጃ እና ሰነድ አዘጋጅ ባለሙያ | አንድ (አነስተኛ) | 1 | በፅሁፍ እና ተመሳሳይ ሙያ | ሌቭል 3 እና ከዛ በላይ | --------- |
| | | ሁለት (ቀላል) | 1 | በፅሁፍ እና ተመሳሳይ ሙያ | ሌቭል 3 እና ከዛ በላይ | ------ |
| | | ሶስት (መካከለኛ) | 1 | በፅሁፍ እና ተመሳሳይ ሙያ | ሌቭል 3 እና ከዛ በላይ | ------ |
| | | አራት (ከፍተኛ) | 1 | በፅሁፍ እና ተመሳሳይ ሙያ | ሌቭል 3 እና ከዛ በላይ | ----- |

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአንድ የምርመራ ተቋም የሚያስፈልጉ የምርመራ መሣሪያዎች ብዛት (ተፈላጊው አነስተኛ ቁጥር) ከዚህ በሠንጠረዥ በተቀመጠው መሠረት ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የመሳሪያ አይነት | ደረጃ አንድ (አነስተኛ) | ደረጃ ሁለት (ቀላል) | ደረጃ ሦስት (መካከለኛ) | ደረጃ አራት (ከፍተኛ) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጎማ ጥርስ መለኪያ Tire Tread Depth gauge | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 2 | የእሳት ማጥፊያ 4 ኪሎግራምPortable Fire Extinguisher | 1 | 2 | 2 | 2 |
| 3 | የመጀመርያ ህክምና እርዳታ(1st aid kit) | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 4 | የመመርመርያ መብራት Inspection Torch | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 5 | Magnifying Lenseየማጉያ መነፅር/ ሌንስ | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 6 | ሲ.ሲ. ቲቪ .ካሜራ አጠቃለይ የምርመራውን ሂደት ቀርፆ ማስቀመጥ የሚችል | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 7 | ጥቅል ሜትርRoll Measuring Tapes | 5 ሜትር | 15 ሜትር | 15 ሜትር | 15 ሜትር |
| 8 | ኮምፒተር / ላፕቶፕ | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 9 | ፕሪንተር | 1 | 1 | 1 | 1 |

## 10. ውክልናው ስለሚቆይበት ጊዜና ስለ ዕድሳት

1) ካሊብሬሽን/የማሽን እርማት/ ወይም ዕድሳት የሚከናወነው ከ ሐምሌ 01 እስከ 15 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ሲሆን በግምገማ ወቅት ካሊብሬት አይደረግም፡፡
2) ውል ተቀባይ የብቃት ማረጋገጫ ማደስ ያለበት ከ ሐምሌ 16 እስከ መስከረም 15 ድረስ ብቻ ነው፡፡



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

3) በዚህ መመሪያ መሠረት ለምርመራ ተቋም የተሰጠ የውክልና ውል የሚቆይበት ጊዜ ውክልናው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን (ለበጀት ዓመቱ) ድረስ ብቻ ነው፡፡
4) ዓመታዊ የተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት ለመስጠት ውክልና የተሰጠው የምርመራ ተቋም በየዓመቱ ውክልናውን ከሰጠው የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮ ቀርቦ ያሳድሳል፡፡
5) የምርመራ ተቋሙ ብቃት ውክልና በሰጠው የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮ ተገምግሞ ብቃቱ ሲረጋገጥ ማንኛውም ውክልና የወሰደ የምርመራ ተቋም በየዓመቱ ከሐምሌ 16 ቀን መስከረም 15 ድረስ የውክልና ውሉን ያሳድሰል፡፡
6) የቴክኒክ ምርመራ ሰርትፍኬት የሚያገለግልበት ጊዜ የምርመራ ሰርትፍኬቱ ከምርመራ ተቋሙ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ለአስራ አምስት ቀናት ብቻ ያገለግላል

## 11. <u>ምርመራን ስለማከናወን</u>

1) ደረጃ አንድ (አነስተኛ) ተሽከርካሪ ምርመራ ተቋም መመርመር የሚችለው የባለ ሁለት እና ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪዎችን እና ጠቅላላ ክብደታቸው እስከ 450 ኪሎ ግራም የሚደርስ ተሽከርካሪዎችን ብቻ ነው፡፡
2) የደረጃ ሁለት (ቀላል) ተሽከርካሪ ምርመራ ተቋም መመርመር የሚችለው ጠቅላላ ክብደታቸው ከ450 እስከ 3,500 ኪሎ ግራም የሚደርስ ተሽከርካሪዎችን ነው፡፡
3) የደረጃ ሶስት (መካከለኛ) ተሽከርካሪ የምርመራ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተጠቀሱት በተጨማሪ ጠቅላላ ክብደታቸው ከ450 እስከ 7500 ኪሎ ግራም ያሉትን ተሽከርካሪዎች መመርመር ይችላል፡፡
4) የደረጃ አራት (ከፍተኛ) ተሽከርካሪ የምርመራ ተቋም ጠቅላላ ክብደታቸው ከ450 ኪሎ ግራም በላይ የሚመዝኑ ተሽከርካሪዎችን፣ እንዲሁም ባለሞተር ጎታችና ግማሽ ተሳቢን፣ ከባድ ካሚዮን እና ተሳቢን መመርመር ይችላል፡፡ ነገር ግን ተጨማሪ ለባለ ሁለት እና የባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪ መመርመሪያ ማሽን መግጠም ከቻለ ጠቅላላ ክብደታቸው እስከ 450 ኪሎ ግራም የሚደርስ ተሽከርካሪዎች መመርመር ይችላል፡፡



እብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

5) በተንቀሳቃሽ የእጅ የምርመራ መሣሪያ እንዲመረምር በውል ሰጪው ፈቃድ የተሰጠው የምርመራ ተቋም ጠቅላላ ክብደታቸው እስከ 450 ኪሎ ግራም የሆነ ማንኛውንም ተሽከርካሪ መመርመር ይችላል፡፡

6) በዚህ በአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተደገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ክብደታቸው ከ450 ኪሎ ግራም በላይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ብቃት በተንቀሳቃሽ የእጅ የምርመራ መሣሪያ መመርመር የሚቻለው ፍቃድ ሰጪው በልዩ ሁኔታ ሲፈቅድ ብቻ ነው፡፡

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከተው ቢኖርም በተንቀሳቃሽ የእጅ የምርመራ መሣሪያ ጠቅላላ ክብደታቸው ከ450 ኪሎ ግራም በላይ ለሆኑት ተሽከርካሪዎች የሚፈቀደው የቴክኒክ ብቃት ምርመራ አገልግሎት የሚውለው ከተፈቀደለት ጊዜ ጀምሮ ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡

8) በተንቀሳቃሽ የምርመራ መሣሪያ በመጠቀም ከቦታ ወደ ቦታ ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ብቃት ምርመራ ማከናወን የሚቻለው ውክልና በሰጠው የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮ እና ውክልና በተሰጠው የምርመራ ተቋም ስምምነት በተዘጋጀ መርሀ-ግብር መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

9) በድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ ወይም ተይዘዉ በልዩ ምርመራ የቴክኒክ ብቃታቸዉ እንዲታይ ውክልና ሰጪው የትራንስፖርት ቢሮ ለሚያቀርበው ጥያቄ ከክፍያ ነፃ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

10) የደረጃ አንድ (አነስተኛ) የተሽከርካሪ የምርመራ ተቋም በአንድ የምርመራ መስመር (Lane) ከሆነ እስከ 72 ተሽከርካሪዎችን ብቻ በአንድ ቀን መመርመር አለበት፡፡

11) የደረጃ ሁለት (ቀላል) ተሽከርካሪ የምርመራ ተቋም በአንድ የምርመራ መስመር (Lane) ከሆነ እስከ 48 ተሽከርካሪዎችን ብቻ በአንድ ቀን መመርመር አለበት፡፡

12) የደረጃ ሶስተኛ (መካከለኛ) ተሽከርካሪ የምርመራ ተቋም በአንድ የምርመራ መስመር (Lane) እስከ 42 ተሽከርካሪዎችን ብቻ በአንድ ቀን መመርመር አለበት፡፡

13) የደረጃ አራት (ከፍተኛ) ተሽከርካሪ የምርመራ ተቋም በአንድ የምርመራ መስመር (Lane) ከሆነ እስከ 42 ተሽከርካሪዎችን ብቻ በአንድ ቀን መመርመር አለበት፡፡

14) የማሽን እርማት ወይም እደሳን /ካሊብሬሽን/ በተመለከተ ከሐምሌ 01 ቀን እስከ 15 ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ሲሆን በግምገማ ወቅት ካሊብሬት እይደረግም፡፡

## 12. ስለ ሥራ ፈቃድ የአገልግሎት ክፍያ

1) ማንኛውም የምርመራ ተቋም የሥራ ፈቃዱን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲወስድ ብር **5000.00** /አምስት ሺ. ብር/ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡
2) ማንኛውም የምርመራ ተቋም የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ማሳደስ ያለበት ከሐምሌ 16 ቀን እስከ መስከረም 15 ቀን ድረስ ብቻ ነው፡፡
3) ማንኛውም የምርመራ ተቋም በየዓመቱ የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ሲያሳድስ፡-
   I. ደረጃ አንድ (አነስተኛ) ወይም ባለ ሁለት እና ባለ ሦስት እግር የተሽከርካሪ ምርመራ ተቋም ከሆነ ለተቋሙ ብር 2000.00/ ሁለት ሺ. ብር/ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡
   II. የደረጃ ሁለት (ቀላል) ወይም ቀላል ተሽከርካሪ የምርመራ ተቋም ከሆነ ለተቋሙ ብር 3000.00 /ሶስት ሺ. ብር/ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡
   III. የደረጃ ሶስት (መካከለኛ) ወይም መካከለኛ የተሽከርካሪ የምርመራ ተቋም ከሆነ ለተቋሙ ብር 4000.00 /አራት ሺ. ብር/ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡
   IV. የደረጃ አራት (ከፍተኛ) ወይም ከፍተኛ ተሽከርካሪ የምርመራ ተቋም ከሆነ ለተቋሙ ብር 5000.00 /አምስት ሺ. ብር/ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡
   V. የሥራ ፈቃድ ወይም የውክልና ውል ዕድሳቱን በወቅቱ ቀርቦ ያላሳደሰ የምርመራ ተቋም መደበኛ የማሳደሻ ጊዜው ካለፈበት ቀን ጀምሮ ለእያንዳንዱ ከማሳደሻ ክፍያው በተጨማሪ ለዘገየበት 15 ቀን 100 ብር በመክፈል ማደስ ይጠበቅበታል፡፡
   VI. የሥራ ፈቃዱን ወይም የውክልና ውሉን በወቅቱ ማሳደስ ያልቻለበት ምክንያት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ መደበኛው የፈቃድ ማደሻ ጊዜ አልፎ በቀጣይ አንድ ወር ውስጥ ውክልና ለሰጠው የትራንስፖርት ቢሮ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
   VII. ውክልና ሰጪው የትራንስፖርት ቢሮ የቀረበለት ምክንያት በቂ ሆኖ ካገኘው ዕድሳቱን ያለ ቅጣት ያከናውናል፡፡

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1



እብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

## 12. ስለ ምርመራ ሰዓት

1) የምርመራ ተቋማት የምርመራ አገልግሎት የሚሰጡበት የሥራ ሰዓት በየቀኑ 8:00 ሰዓት ይሆናል፡ ከዚህ ዉጪ መስራት የሚፈልግካለ ተጨማሪ የሰዉ ሃይል እንዲሁም የሚሰራበትን የሚሰራበትን የስራ ሰአት ለፍቃድ ሰጪዉ አካል በቅድሚያ ያሳዉቃል፡፡
2) የማታ ለመስራት የማታ መስፈርት መሟላት እና ውክልና ከሠጠው አካል የስራ ሰዓት ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡
3) በማታው ክፍለ-ጊዜ አገልገሎት ለመስጠት የሚፈልግ የምርመራ ተቋም በቅድሚያ ከፈቃድ ሰጪው አካል ፈቃድ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡
4) የማታ አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ተቋም በቀን ለሚሰሩ የተቀመጠዉን የሰው ሀይል በእጥፍ ማሟላት አለበት፡፡

## 13. የምርመራ ተቋም ስለሚያስከፍለው የአገልግሎት ክፍያ

1) ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ባለ ሁለት ወይም ደብል ጋቢና ተሽከርካሪዎች ከ1 እስከ 12 መቀመጫ ባላቸዉ ሥር ይካተታሉ፡፡
2) ማንኛውም የምርመራ ተቋም ከዚህ በታች በተመለከቱት ሠንጠረዦች በተቀመጠው የክፍያ መጠን መሠረት ለመጀመሪያ ምርመራ ከተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ተሽከርካሪውን ካስመረመረው አካል የምርመራ አገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፡፡

### ሀ) ለህዝብ ትራንስፖርት በመቀመጫ

| ተ.ቁ | የህዝብ ትራንስፖርት (በመቀመጫ) | አዲስ ታሪፍ በብር |
|---|---|---|
| 1 | 1-12 | 350 |
| 2 | 13-29 | 370 |
| 3 | 30-44 | 406 |
| 4 | 45 በላይ | 430 |
| 5 | ሞተር ሳይክልና ባለ ሶስት እግር ተሽከርካሪ | 250 |



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

ለ) የጭነት ትራንስፖርት በኩንታል

| ተ.ቁ | የጭነት ትራንስፖርት(በኩንታል) | አዲስ ታሪፍ በብር |
|---|---|---|
| 1 | 1-15 | 350 |
| 2 | 16-40 | 370 |
| 3 | 41-69 | 394 |
| 4 | 70-120 | 416 |
| 5 | 121 እና በላይ200 | 439 |
| 6 | 201-350 | 464 |
| 7 | 351- በላይ | 488 |
| 8 | ፓወር ፕላስ ሀይቤድ /ሎቤድ | 495 |
| 9 | ተሳቢ ብቻዉን ተነትቶ ሲመጣ | 320 |
| 10 | ልዩ ተንቀሳቃሽ | 375 |

ሐ) የፈሳሽ የጭነት ትራንስፖርት በሊትር

| ተ.ቁ | የፈሳሽ የ ጭነት ትራንስፖርት በሊትር | አዲስ ታሪፍ በብር/ |
|---|---|---|
| 1 | እስከ 1560 | 350 |
| 2 | 1561-4160 | 372 |
| 3 | 4161-7176 | 394 |
| 4 | 7177-12480 | 416 |
| 5 | 12481 እና በላይ | 440 |

3) የመጀመሪያ ምርመራ ወድቀው እንደገና ተስተካክለው ለድጋሚ ምርመራ በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተመልሰው የሚቀርቡ ከሆነ ቀጥሎ የተዘረዘረውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል የወደቁበትን ብቻ ያስመረምራሉ፡፡



እብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia Transport Authority No. 1

## ሀ) የህዝብ ትራንስፖርት በመቀመጫ

| ተ.ቁ | የህዝብ ትራንስፖርት (በመቀመጫ) | የወደቁበትን የተሽከርካሪ ክፍል አስተካክለው በድጋሚ ሲመረመሩ | |
|---|---|---|---|
| | | የፍሬኖች (እጅና የእግር) ብቃት የግንባር መብራቶች አቅጣጫና መጠን | የእይታ ምርመራ (Visual Inspection) ብር |
| | | አዲሱ 60 ፐርሰንት ከታሪፉ ውጪት | አዲሱ 40 ፐርሰንት ከታሪፉ ውጤት |
| 1 | 1-12 እና ደብል ገቢና | 210.00 | 140.00 |
| 2 | 13-29 | 222.00 | 148.00 |
| 3 | 30-44 | 243.60 | 162.40 |
| 4 | 45 እና በላይ | 258.00 | 172.00 |
| 5 | ሞተር ሳይክልና ባለ ሶስት እግር ተሽከርካሪ | 150.00 | 100.00 |

## ለ) የደረቅ ጭነት ትራንስፖርት በኩንታል

| ተ.ቁ | የደረቅ ጭነት ትራንስፖርት (በኩንታል) | የወደቁበትን የተሽከርካሪ ክፍል አስተካክለው በድጋሚ ሲመረመሩ | |
|---|---|---|---|
| | | የፍሬኖች (የእጅና የእግር) የግንባር መብራቶች አቅጣጫና መጠን ብቃት ብር | የእይታ ምርመራ (Visual Inspection)ብር |
| | | አዲሱ | አዲሱ |
| 1 | 1-15 | 210.00 | 140.00 |
| 2 | 16-40 | 222.00 | 148.00 |
| 3 | 41-69 | 236.40 | 157.60 |
| 4 | 70-120 | 249.60 | 166.40 |
| 5 | 121 እና በላይ200 | 263.40 | 175.60 |
| 6 | 201-350 | 278.40 | 185.60 |
| 7 | 351- በላይ | 292.80 | 195.20 |
| 8 | ፓወር ፐላስ ሀይቤድ /ሎቤድ | 297.00 | 198.00 |
| 9 | ተሳቢ ብቻዉን ተጎቱቶ ሲመጣ | 192.00 | 128.00 |
| 10 | ልዩ ተንቀሳቃሽ | 225.00 | 150.00 |



እብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

## ሐ) የፈሳሽ ጭነት ትራንስፖርት በሊትር

| ተ.ቁ | የፈሳሽ ትራንስፖርት (በሊትር) | የወደቁበትን የተሽከርካሪ ክፍል አስተካክለው በድጋሚ ሲመረመሩ ብር | |
|---|---|---|---|
| | | የፍሬኖች ( እጅና የእግር) ብቃት ብር የግንባር መብራቶች አቅጣጫና መጠን | የእይታ ምርመራ ብር |
| | | አዲሱ | አዲሱ |
| 1 | እስከ 1560 | 210.00 | 140.00 |
| 2 | 1561-4160 | 223.20 | 148.80 |
| 3 | 4161-7176 | 236.40 | 157.60 |
| 4 | 7177-12480 | 249.60 | 166.40 |
| 5 | 12481 እና በላይ | 264.00 | 176.00 |



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14.የተከለከሉ ተግባራት

1) ድርጅቱም ሆነ ሠራተኞቹ ከአገልግሎት ክፍያ ውጭ ከተገልጋዩ የገንዘብም ሆነ የማቴሪያል ስጦታ ወይም ያልተገባ ጥቅም መጠየቅ የተከለከለ ነው፡፡
2) ለማንኛውም ተሽከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ወቅት በቅድሚያ በዕይታ ምርመራ ሳይደረግለት የማሽን ምርመራ ማከናወን ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡
3) በአካል ላልቀረበ ተሽከርካሪ ወይም ተመርምሮ ብቁ ላልሆነ ተሽከርካሪ መርማሪ ባለሙያው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲያዘጋጅ ማስገደድ የተከለከለ ነው፡፡
4) ስለ ሰጠው የምርመራ አገልግሎት የያዛቸውን መረጃዎች ውክልና ከሰጠው አካል እውቅና ውጭ ለሌላ ወገን አሳልፎ መስጠት አይችልም፡፡
5) ማንኛውንም ተሽከርካሪ ለደረጃው የተመደበውን ተገቢውን የመመርመሪያ መሣሪያ ሙሉ ለሙሉ ሳይጠቀሙ መመርመር ክልክል ነው፡፡
6) ማንኛውም የምርመራ ተቋም በተፈቀደለት የብቃት ደረጃ እና ተወስኖ በተሰጠዉ ቦታና ጊዜ ውጪ መመርመር የለበትም፡፡
7) ለማንኛውም የምርመራ ተቋም በጊዜና በቦታ ተለይቶና ተወስኖ ከተሰጠው ውጪ በተንቀሳቃሽ የእጅ የምርመራ መሣሪያ መመርመር የተከለከለ ነው፡፡
8) ማንኛውም የምርመራ ተቋም በጊዜና በቦታ ተለይቶና ተወስኖ የተሰጠውን በተንቀሳቃሽ የእጅ የምርመራ መሣሪያ ወይም በተንቀሳቃሽ የምርመራ መሣሪያ የመመርመሪያ ፈቃድ በሌላ ጊዜና ቦታ መጠቀም አይችልም፡፡
9) የምርመራ ተቋማት የትርፍ ጊዜ /የኦቨር ታይም/ የምርመራ አገልግሎት መስጠት ክልክል ነው፡፡

### 15. ውክልና ስለሚነሣበት ሁኔታ

የማንኛውም የምርመራ ተቋም ውክልና ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊነሣ ይችላል፡፡

ሀ) በመስፈርቱ መሠረት አሟልቶ አገልግሎቱን ሳይሰጥ ከቀረ፣



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትራንስፖርት ባለሥልጣን
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No 1

ለ) ተቋሙ በሰጠው የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ ሥራ የአሰራር ብቃትና ጥራት ማጣት የሚመረምራቸው ተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ብቃት ደረጃ የተሟላ ሆኖ ካልተገኘና ይህም በሚደረግ የቁጥጥርና የግምገማ ሥራዎች ባለስልጣኑ እና/ወይም ውክልና ሰጭ በመደባቸው ባለሙያዎች ከተረጋገጠና በተሽከርካሪ ቴክኒክ ብቃት ላይ የሚኖረው ቀጣይ ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ፣

ሐ) በአዋጅ ቁጥር 681/2002 እና በዚህ መመሪያ የተጣሉበትን ግዴታዎችን ሳያሟላ ሲቀር፣

መ) የተሰጠውን ውክልና ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ ሰጥቶ የተገኘ እንደሆነ፣

ሠ) ይህን መመሪያ ያልተከተለ ምርመራ አከናውኖ ከተገኘ፣

ረ) አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ስራ ከጀመረ በኋላ አጓድሎ ከተገኘ፣

ሰ) ውክልና በሰጠውና ውክልና በተሰጠው የምርመራ ተቋም መካከል በሥራ ሂደት አለመግባባቶች ሲፈጠር፡፡

## 16.የቅጣት እርምጃ አወሳሰድ

1) ማንኛውም የምርመራ ተቋም ለምርመራው እውቅና በተሰጠበት ዋናው መሥሪያ ቤትም ሆነ በቅርንጫፍ ቤቱ ተገቢውን ምርመራ ሳያከናውን የሐሰት የምስክር ወረቀት በመስጠት ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ ወይም ከተሰጠው ደረጃ በላይ ሲሰራ የተገኘ እንደሆነ፡

   ሀ) ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋቱን እንዲያስተካክል ተደርጎ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

   ለ) ለሁለተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ጥፋት ከፈፀመ የተቋም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬቱ ለ 3 ወር እንዲታገድ ይደረጋል፡፡

   ለ) ለሦስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ጥፋት የተቋም ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለ 6 ወር ይታገዳል፡፡

   ሐ.ለአራተኛ ጊዜ ይህንኑ ጥፋት ፈፅሞ ከተገኘ በወንጀል መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የብቃት ማረጋገጫው ሰርተፍኬቱ ይሰረዛል።



እብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

## የጥፋት ዓይነቶች እና ለጥፋቱ የተቀመጡ ቅጣቶች

| ተ.ቁ | የጥፋት ዝርዝር | ተጠያቂ | የሚወሰድ እርምጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት | በ2ኛ ጊዜ ጥፋት | በ3ኛ ጊዜ ጥፋት | በ4ኛ ጊዜ ጥፋት |
| 1 | ከተቀመጠዉ የአገልግሎት ክፍያ በላይ አስከፍሎ መገኘት | የምርመራ ተቋሙ | የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያና የክፍያውን ልዩነት እንዲመልስ እና 1000 ብር ቅጣት ለመንግሥት እዲከፍል ይደረጋል | የደብዳቤ ይፃፍበታል የክፍያውን ልዩነቱ እንዲመልስ እና 5000 ብር ቅጣት ለመንግስት እዲከፍል ይደረጋል | ለ3 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ፈቃ ዱን መሰረዝ |
| 2 | በትራንስፖርት ባለሥልጣን የምርመራ ቼክ ሊስት መሠረት የዓመታዊ ምርመራ አገልግሎት አለመስጠት | የምርመራ ተቋሙ | የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ለድርጅቱ በመስጠት 3000.00 ብር ቅጣት | ለ3 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ፈቃዱን መሰረዝ |
| | | መርማሪ ባለሙያ | ጥፋት የፈጸመው መርማሪ ባለሙያ የመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያና | ጥፋት የፈጸመው መርማሪ ባለሙያ 3000 ብር ቅጣት እና ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል | ለ3 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ፈቃዱን መሰረዝ |

አብዲሣ ያደታ ሙሳ
ዋና ዳይሬክተር

| ተ.ቁ | የጥፋት ዝርዝር | ተጠያቂ | የሚወሰድ እርምጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት | በ2ኛ ጊዜ ጥፋት | በ3ኛ ጊዜ ጥፋት | በ4ኛ ጊዜ ጥፋት |
| 3 | የተሽከርካሪው መረጃዎች ከተሽከርካሪው አካል ላይ፡ከባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር እና ከምርመራ ሰርተፍኬት ጋር ልዩነት ከተፈጠረ | የምርመራ ተቋሙ | የመጨረሻ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት | ጥፋት ተቋም3000ብር ቅጣት እናማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል | ለ3 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ6ወር ከአገልግሎት ማገድ |
| | | መርማሪ ባለሙያ | ለባለሙያው የመጨረሻ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያና የከደመወዙ 1000ብር ቅጣት ለመንግሰት ገቢ ያደርጋል፡፡ | ለ3 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | የብቃት ማረጋጫውን መሰረዝ |
| 4 | ተሽከርካሪ ቀርቦ ሳይመረመር የዓመታዊ ምርመራ መረጃ መስጠት (ጉዳዩ ተጣርቶ ሲረጋገጥ) | የምርመራ ተቋሙ | ፈቃዱን መሰረዝ | | | |
| | | መርማሪ ባለሙያ | የብቃት ማረጋጫውን መሰረዝ | | | |
| | ብቃት የሌላቸውን ተሽከርካሪዎች የምርመራ ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ማድረግ (ጉዳዩ ተጣርቶ ሲረጋገጥ) | የምርመራ ተቋሙ | ፈቃዱን መሰረዝ | | | |
| | | መርማሪ ባለሙያ | የብቃት ማረጋጫውን መሰረዝ | | | |

አብዲሣ ያደታ ሙሉታ
ዋና ዳይሬክተር

| ተ.ቁ | የጥፋት ዝርዝር | ተጠያቂ | | የሚወሰድ እርምጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት | በ2ኛ ጊዜ ጥፋት | በ3ኛ ጊዜ ጥፋት | በ4ኛ ጊዜ ጥፋት |
| 6 | የምርመራው ስራ ተገቢውን የብቃት ማረጋገጫ በሌለው ባለሙያ አገልግሎት መስጠት | የምርመራ ተቋሙ | | ለ6 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ | |
| 7 | የምርመራ ቅደም ተከተልን ሳይጠብቅ ወይም የእይታ ምርመራን ያላከናወነና ብቃቱን ያላረጋገጠ ተሽከርካሪን በማሽን ሲመረምር የተገኘ | የምርመራ ተቋሙ | | የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ | የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እና 3000.00 (ሦስት ሺ. ብር) ይቀጣል፡፡ | 6 ወር ከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ |
| | | መርማሪ ባለሙያ | | የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ | የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እና 1000.00 (አንድ ሺ. ብር) ይቀጣል፡፡ | የሙያ ፈቃድ መሰረዝ | |
| 8 | በመመሪያውመሠረትየብቃት ማረጋገጫው በወሰደበት አግባብ የነበረውን መሣሪያ አጓድሎ አገልግሎት መስጠት | የምርመራ ተቋሙ | ፍሬንእና ሳይድ ስለፕ | የተጓደለው ከሆነ ለ4 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | 6 ወር ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ |
| | | | መብራት እና ጭስ | ለ2 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ4 ወር ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ |

አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

| ተ.ቁ | የጥፋት ዝርዝር | ተጠያቂ | | የሚወሰድ እርምጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት | በ2ኛ ጊዜ ጥፋት | በ3ኛ ጊዜ ጥፋት | በ4ኛ ጊዜ ጥፋት |
| | | መርማሪ ባለሙያ | ፍሬን ሳይድ ስለፕ | የተጓደለው ከሆነ ለ6 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ፍቃዱን መሰረዝ | |
| | | | መብራት እና ጭስ | ለ3ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ5 ወር ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ |
| 9 | በመመሪያው መሠረት የብቃት ማረጋገጫው በወሰደበት አግባብ የነበረውን የሰው ኃይል አንድሎ አገልግሎት መስጠት | የምርመራ ተቋሙ | | የተጓደለው ሰዉ 1 ከሆነ ከሆነ ለተከታታይ አንድ /1/ ወር ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ3 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ6 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ |
| | | | | የተጓደለው ሰዉ 2 ከሆነ ከሆነ ለተከታታይ ሶስት /3/ ወር ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ6ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ |
| 10 | የብቃት ማረጋገጫ ሲወሰድ ከነበሩት ባለሙያዎች ውጪ ለፍቃድ ሰጪው መስርያቤት ሳያሳውቅ ሲያሰራ ገተገኘ | የምርመራ ተቋሙ | | ለ6 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ | |

አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

| ተ.ቁ | የጥፋት ዝርዝር | ተጠያቂ | የሚወሰድ እርምጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት | በ2ኛ ጊዜ ጥፋት | በ3ኛ ጊዜ ጥፋት | በ4ኛ ጊዜ ጥፋት |
| 11 | በማንኛዉም እገዳ ወቅት አገልግሎት መስጠት | የምርመራ ተቋሙ | ከአገልግሎት መሰረዝ እና በህግ እንዲጠየቅ ማድረግ | | | |
| | | መርማሪ ባለሙያ | ከአገልግሎት መሰረዝ እና በህግ እንዲጠየቅ ማድረግ | | | |
| 12 | የምርመራ አገልግሎት ለሰጣቸው ተሽከርካሪዎች አገልግሎቱን እንደፈፀመ ለመለያ የሚሆን የተቋሙን ስምና አድራሻ የሚያሳይ ተለጣፊ ምልክት በግንባር መስታወት ላይ ያለማድረግ፡፡ | የምርመራ ተቋሙ | በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት | ለ1 ወር ከአገልግሎት ማገድ | ለ3 ተከታታይ ወራት ማገድ | ለ6 ተከታታይ ወራት ማገድ |
| | | መርማሪ ባለሙያ | በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት | ለ1 ወር ከአገልግሎት ማገድ | ለ3 ተከታታይ ወራት ማገድ | ለ6 ተከታታይ ወራት ማገድ |
| 13 | ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ ያለመስጠት | የምርመራ ተቋሙ | በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት | ለ3 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ6 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ |
| 14 | የአገልግሎት አሰጣጡን አስመልክቶ ውል ሰጭ | የምርመራ ተቋሙ | ለ2 ተከታታይ ወራት አገልግሎት | ለ3 ተከታታይ ወራት አገልግሎት | ለ6 ተከታታይ | ለ1 ዓመት አገልግሎት |

አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

| ተ.ቁ | የጥፋት ዝርዝር | ተጠያቂ | የሚወሰድ እርምጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት | በ2ኛ ጊዜ ጥፋት | በ3ኛ ጊዜ ጥፋት | በ4ኛ ጊዜ ጥፋት |
| | ለሚያቀርበው ጥያቄ በ2 የስራ ቀናት ውስጥ ዝርዝር ማብራሪያ ከነመረጃው ያለመስጠት | | ማገድ | ማገድ | ወራት አገልግሎት ማገድ | ማገድ |
| 15 | በተሰጠው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ መሰረት ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት ለውል ሰጭው ያለማቅረብ | የምርመራ ተቋሙ | በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት /2000 ሁለት ሺ.ህ ብር ቅጣት ለመንግስት ገቢ ማድረግ | ለ3 ተከታታይ ወራት አገልግሎት ማገድ | ለ6 ተከታታይ ወራት አገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ |
| 16 | ከጸታ ቤዙ ላይ እያወጡ ላልተመረመረ ተሽከርካሪ ዉጤት መስጠት | የምርመራ ተቋሙ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ | | |
| | | መርማሪ ባለሙያ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | | | |
| 17 | የጸታ ቤዙን ምስጢር ቁጥር ከተፈቀደለት ባለሥልጣን መስሪያ ቤት ውጪ የነካና የተጠቀመ | የምርመራ ተቋሙ | ለ6 ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ | |
| 18 | የመረመራቸውን ተሽከርካሪዎች የሚመለከት የተሟላ መረጃ በIT፣ በሰነድ | የምርመራ ተቋሙ | በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት | ለ6 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ |

አብዲሣ ያደታ መኮንን
ዋና ዳይሬክተር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

| ተ.ቁ | የጥፋት ዝርዝር | ተጠያቂ | የሚወሰድ እርምጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት | በ2ኛ ጊዜ ጥፋት | በ3ኛ ጊዜ ጥፋት | በ4ኛ ጊዜ ጥፋት |
| | (Hard Copy) መዝግቦ ያለመገኘት | | | ማገድ | | |
| 19 | የተመረመረዉ ተሽከርካሪ በዳታ ቤዝ የማገኝ ከሆነ | የምርመራ ተቋሙ | ለ3 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ እና 10000 /አስር ሺ ብር ቅጣት/ | ለ6 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ለ1 ዓመት ከአገልግሎት ማገድ | ፈቃዱን መሰረዝ |
| 20 | ከአንድ ዓመት በፊት ውክልና ለሰጠው የትራንስፖርት ቢሮ ሳያሳውቁ አገልግሎቱን ማቋረጥ | የምርመራ ተቋሙ | አግባብ ባለው ወንጀለኛ ህግ ይጠየቃል | | | |
| 21 | ከውል ሰጭው የተሰጠውን የአገልግሎት ሰጭነት ማስረጃና የስራ ሂደቱን መግለጫ በግልፅ ቦታ ለተገልጋዮች ያለመለጠፍ | የምርመራ ተቋሙ | በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት | ለ1 ወር ከአገልግሎት ማገድ | ለ3 ተከታታይ ወራት ከአገልግሎት ማገድ | ፈቃዱን መሰረዝ |
| 22 | የዘመኑን/የዓመቱን ፍቃድ ሳያድስ አገልገሎት ሲሰጥ የተገኘ | የምርመራ ተቋሙ | የቀጣዩን 1 ዓመትከአገልግሎት ማገድ | ከአገልግሎት መሰረዝ | | |
| 23 | ከመስፈርቱ/ከስታዳርድ ውጪ ፍቃድ የሰጠ ባለሙያ | ትራንስፖርት ባለስልጣን /ክልል ትራ/ ቢሮ | በትራንስፖርት ባለስልጣን | | | |



እብዲሣ ያደታ ሙላታ
ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትራንስፖርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport

| ተ.ቁ | የጥፋት ዝርዝር | ተጠያቂ | የሚወሰድ እርምጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት | በ2ኛ ጊዜ ጥፋት | በ3ኛ ጊዜ ጥፋት | በ4ኛ ጊዜ ጥፋት |
| | | | ለዲሲፒሊን ቀርቦ ይቀጣል | | | |
| 24 | በቼክ ሊስቱ መሰረት ግምገማ ወይም ቁጥትር ያልፈፀመ ባለሙያ | ትራንስፖርት ባለስልጣን/ ክልል ትራ/ ቢሮ | በትራንስፖርት ባለስልጣን ክልል ትራ/ ቢሮ ለዲሲፒሊን ቀርቦ ይቀጣል | | | |
| 25 | የፍቃድ ሰጪ ባለሙያ ከፍቃድ ተቀባዩ ጋር ሕገ-ወጥ ሥራ ከሠራ | ሁለቱም በህግ ይጠየቃሉ | | | | |
| 26 | የውክልና ሰጪውን ፈቃድ ሳያገኝ ወይም የአሰራር መመሪያውን ሳይከተል በከፊል ተንቀሳቃሽ መሣሪያ መርምሮ የተገኘ ተቋም | የምርመራ ተቋሙ | ፈቃዱ ይሰረዛል | | | |
| 27 | የፍቃድ ሰጪ አካልን ዳታ ቤዝ ክራክ አርጎ ወይም መረጃ ከዳታ ቤዙ ከወሰደ የመርመራ ተቋሙ | የምርመራ ተቋሙ | ሶስት ወር ከስራ ይታገዳል | ስድስት ወር ከስራ ይታገዳል | አንድ አመት ማገድ | ፍቃድ መሰረዝ |



ኢብዲሣ ያያታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

| ተ.ቁ | የጥፋት ዝርዝር | ተጠያቂ | የሚወሰድ እርምጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት | በ2ኛ ጊዜ ጥፋት | በ3ኛ ጊዜ ጥፋት | በ4ኛ ጊዜ ጥፋት |
| 28 | በድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ ወቅት የምርመራ ተቋሙ ከእስታዳርድ በታች ለሆኑ ተሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ሰጥቶ ሲገኝ | የምርመራ ተቋሙ | 250000/ሀያ አምስት ሺ.ህ ብር ቅጣት ይቀጣል | 500000/ሀምሳ አምስት ሺ.ህ ብር ቅጣት ይቀጣል | አንድ አመት ማገድ | ፍቃድ መሰረዝ |
| | | መርማሪ ባለሙያ | ሶስት ወር ከስራ ይታገዳል | ሶስት ወር ከስራ ይታገዳል 10000/አስር ሺ. ይቀጣል | አንድ አመት ማገድ | ፍቃድ መሰረዝ |
| 29 | የምርመራ ሳያደርግ ከትራንስፖርት ባለስልጣን ቦሎ የሰጠ የትራንስፖርት ባለሙያ | በትራንስፖርት ባለስልጣን | ለዲሲፒሊን ቀርቦ ይቀጣል የዲስፕሊን መመርያ መሰረት ይቀጣል/ትቀጣለች | | | |
| 30 | እስፒድ ሊሚተር/ የፍጥነት መግቻ/ ያልገጠመ ተሽከርካሪ ሳይኖረዉ ያሳለፈ | የምርመራ ተቋሙ | ሶስት ወር ከስራ ይታገዳል | ሶስት ወር ከስራ ይታገዳል | ስድስት ወር ከስራ ይታገዳል | ፍቃድ መሰረት |
| | | መርማሪ ባለሙያ | ሶስት ወር ከስራ ይታገዳል | ሶስት ወር ከስራ ይታገዳል | ስድስት ወር ከስራ ይታገዳል | ፍቃድ መሰረት |

## 17. ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዙ ማንዋሎች የመመሪያው አካል በመሆን ተፈፃሚ ይሆናሉ

## 18. የቅጣት አወሳሰድና ቆይታ ጊዜ

1) የአንድ ጥፋት ቅጣት ሪከርድ ሆኖ የሚቆየው ለሁለት ተከታታይ ዓመት ይሆናል፡፡
2) በድጋሚ ለሚፈፀም ጥፋት ለእርከኑ የተቀመጠዉን የመጨረሻ ከባድ የቅጣት እርምጃ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3) ከላይ የተዘረዘሩት የስነስረዓት እርምጃ እንደተጠበቁ ሆነው እንደ ጥፋቶቹ ደረጃ አግባብነት ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ሊጠየቅ ይችላል፡፡

## 19. ስለ ቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ሥርዓት

1) ማንኛውም ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታው በተፈጠረ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለምርመራ ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል፡፡
2) የምርመራ ተቋሙ የበላይ ኃላፊ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው ተገቢውን ምላሽ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡
3) በምርመራ ተቋሙ የበላይ ኃላፊ በተሰጠው ምላሽ ያልረካ ከሆነ የምርመራ ተቋሙ የበላይ ኃላፊ ምላሽ በሰጠ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ውክልና ለሰጠው የክልል ትራንስፖርት ቢሮ የበላይ ኃላፊ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡
4) የክልሉ የትራንስፖርት ቢሮ የበላይ ኃላፊ ጉዳዩን አጣርቶ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ውሳኔ ይሰጣል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ቅሬታ በፈጠረው የምርመራ ተቋም ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
5) የክልሉ ትራንስፖርት ቢሮ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡
6) በተሰጠው የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ በተሰጠ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

## 20.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

ከዚህ በፊት የቴክኒክ ምርመራ ስራዎችን በውክልና ሲሰሩ የነበሩ የምርመራ ተቋማት በዚህ መመሪያ መሠረት ከሚመለከተው የትራንስፖርትወይም የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ እንደገና ውክልና ወስደው ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

## 21. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ይህንን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 22. <u>ስለተሻረ መመሪያ</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጻረሩ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች እና አሰራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

## 23. <u>መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከነሐሴ ----------ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አብዲሳ ያደታ

የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር

አብዲሳ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር